# ይረገም !

ይረገም ምላሴ፣
ብርሃኑ፣ ብርቱካን ብሎ የጮኸበት
ይረገም ይህ እግሬ፣
በጥልቁ በረዶ ሰልፍ የኳተነበት
ይረገም ይህ እጄ፣
ጀግኖች መጡ ብሎ ገንዘብ የጣልኩበት
ይረገም ይህ ዓይኔ፣
የታማኝን ቲቪ አፍጥጦ ያየበት
ይረገም ይህ ጆሮዬ፣
የባንዳ ሬዲዮኖችን ያደማመጠበት
ይሰበር ይህ ማውሴ፣
ኢትዮ ሪቪውን ክሊክ ያረገበት
ያ ህሊናዬማ፣ ገና ጉድ አለበት
ሁሉንም ለቃቅሞ ያልተቃወመበት
ሚዛን እስኪደፋ የወላወለበት።

ሰፊው እውነት ሳለ የሚጠየቅበት
በቅራሚ ወሬ፣ የተታለልኩበት
አገሬን ለማፍረስ ሲደላልቱባት
ቤቴም ታዘበችኝ የተከተትኩባት
በዓይን አፋር ይሉኝታ የተያዘው አፌ
ምን ላውርስ ለልጆቼ ለማይቀር ማለፌ
የዕድሜ ልክ ባርነት? አይን አውጣ ባንዳነት?
ወይንስ ነፃነት፣ ኩሩ ኢትዮጵያዊነት።

ይቅር በይኝ አገሬ፣ ገድዬሽ አልበላም
ለእውነት ልሞት ቆረጥኩ በሌሎች ብጠላም
መቼም ኢትዮጵያን ያለ ይጠላል በባንዳ
ለእኔ ይሻለኛል ከዘላለም ጸጸት ከህሊና ዕዳ
እምቢ ለጐሰኛው፣ እምቢ ለወያኔ
ኢትዮጵያን እናድን፣ ነቃ በል ወገኔ
አንድነቷን ብሏል ጀግናው ኃይሉ ሻውል
ተከትዬው ልጓዝ ዛሬ ነገ ሳልል፡፡

ከሚካኤል ሰይፉ (ቶሮንቶ፤ካናዳ)